# የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ማስፈፀሚያ ረቂቅ የአሠራር ደንብ

መስከረም 2018 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

## ማውጫ


መግቢያ ........................................ 1

**ክፍል አንድ**
**ጠቅላላ**

1. አጭር ርዕስ ........................................ 1
2. ትርጓሜዎች ........................................ 1
3. የአሠራር ደንቡ ዓላማ ........................................ 2

**ክፍል ሁለት**
**የቦርድ አባላት ብዛትና ስብጥር**

4. የቦርድ አባላት ብዛት ........................................ 2
5. የቦርድ ስብጥር ........................................ 2

**ክፍል ሦስት**
**የጊዜያዊ ቦርድ ዕጩዎች ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

6. ጊዜያዊ የቦርድ ዕጩዎች ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ........................................ 3
7. የጊዜያዊ ኮሚቴው የሥራ ማብቂያ ጊዜ ........................................ 3

**ክፍል አራት**
**በቦርድ አባላት የዕጩዎች ጥቆማና ምርጫ ሂደት የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት**

8. በሥራ ላይ ያለው ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት ........................................ 3
9. የቦርድ የዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ ተግባርና እና ኃላፊነት ........................................ 4
10. የጊዜያዊ የዕጩዎች ምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ ተግባርና እና ኃላፊነት ........................................ 4
11. የማህበሩ ፀሐፊ ተግባርና እና ኃላፊነት ........................................ 4

**ክፍል አምስት**
**ውክልና**

12. በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በውክልና ስለመሳተፍ ........................................ 5
13. የውክልና ሠነድ ስለማቅረብ ........................................ 5

## ክፍል ስድስት
## የቦርድ ዕጩዎች ጥቆማ እና ምርጫ ሂደት

14. አጠቃላይ ....................5
15. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ምልመላ ....................6
16. የአጠቃላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ (General Director) አባላት ጥቆማ ....................6
17. ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች በዕጩነት ስለመጠቆም ....................6
18. የዕጩዎች ጥቆማ ስለመቀበል ....................6
19. ለምርጫ የሚቀርቡ የዕጩዎች ዝርዝር ....................7
20. ድምጽ የመስጠት ሥነ-ሥርዓት ....................7
21. የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ....................8
22. ድምጽ ስለመስጠት ....................8
23. ድምጽ የተሰጠባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የሚሰበሰቡበት መንገድ ....................8
24. የድምጽ ቆጠራ ....................8
25. የምርጫ ውጤት ስለማሳወቅ እና የውጤት ማስተካከያ ስለማድረግ ....................9
26. የእኩል ድምጽ ውጤት ሲኖር የሚተገበረው የመፍትሄ ሂደት ....................10
27. የምርጫ ውጤት ስለማሳወቅ ....................10
28. የተጠባባቂዎች ዝርዝር ....................10
29. የምርጫ ውጤት በጉባዔው ቦታና ቀን ማሳወቅ አለመቻል ....................10
30. የምርጫ ሂደት ሠነዶች ስለማስቀመጥ ....................10

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

31. የሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነት ....................11
32. ማሻሻያ ....................11
33. የተሻረ ደንብ ....................11
34. የአሠራር ደንቡ ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን ....................11

## መግቢያ

ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ማስፈፀሚያ የአሠራር ደንብ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ለመጠቆም እና ለመምረጥ ግልጽ እና ጥብቅ የሆነ አሠራር ለመዘርጋት ያወጣውን መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 እና SBB/89/2024፣ እንዲሁም የአቢሲንያ ባንክ አ.ማ. የተሻሻለውን የመመሥረቻ ጽሑፍ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ሠነድ "**የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ማስፈፀሚያ የአሠራር ደንብ**" ተብሎ የሚጠቀስ ሲሆን፤ ከዚህ በኃላ "**የአሠራር ደንብ**" እየተባለ ይጠራል፡፡

### 2. ትርጓሜዎች

በዚህ የአሠራር ደንብ ውስጥ የሚከተሉት ቃላት ከዚህ በታች የተመለከቱት ትርጓሜዎች ይኖራቸዋል፡-

2.1. "**ቦርድ**" ማለት የአቢሲንያ ባንክ አ.ማ ቦርድ ነው፡፡

2.2. "**አጠቃላይ ዳይሬክተር** (General Director)" ማለት የባንኩ ባለአክሲዮን የሆነና በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ ገለልተኛ ዳይሬክተር (Independent Director) መደብ ውስጥ ያልተመደበ የቦርድ አባል ነው።

2.3. "**ገለልተኛ ዳይሬክተር** (Independent Director)" ማለት በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ ሆኖ የባንኩ የአክሲዮን ባለቤት ያልሆነ ፣ በባንኩ በማንኛውም የዕለት ከዕለት አስተዳደር ውስጥ የማይሳተፍ ፣ ነጻ እና ሚዛናዊ አስተያየት ከሚያዛቡ ማንኛውም ዓይነት ውስጣዊ፣ ውጫዊ፣ የፖለቲካና ከሌሎችም ተጽዕኖዎች ነጻ የሆነ እና በዚህ የአሠራር ደንብ መሰረት የተመረጠ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፡፡

2.4. "**ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን**" ማለት ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የያዘው አክሲዮን ሁለት በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ባለአክሲዮን ነው፡፡

2.5. "**ተጽዕኖ የሌለው ባለአክሲዮን**" ማለት ከባንኩ ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል ውስጥ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የያዘው የአክሲዮን ድርሻ ከሁለት በመቶ በታች የሆነ ባለአክሲዮን ነው፡፡

2.6. "**የተጠባባቂ ዝርዝር** (Waiting list)" ማለት ድምጽ ያገኙ ነገር ግን ያልተመረጡ የቦርድ አባላት ዕጩዎችን ስም ዝርዝር የያዘ ሲሆን፤ በቦርዱ የስራ ዘመን ውስጥ ክፍት የቦርድ መደቦች ሲኖሩ ብቁ የሆኑ ዕጩዎች ባገኙት ድምጽ እና ሕጋዊ መስፈርቶች መሠረት ክፍት ቦታ ለመሙላት የተዘጋጀ ነው፡፡

2.7. "**የዕጩዎች የምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ** (Nomination and Remuneration Board Committee)" ማለት ለገለልተኛ ዳይሬክተር ቦታዎች ዕጩዎችን መለየት፣ መገምገም እና የዕጩዎችን ዝርዝር አዘጋጅቶ ለቦርድ የማቅረብ ኃላፊነት ያለው የባንኩ ቦርድ ኮሚቴ ነው።

2.8. "**የጊዜያዊ የዕጩዎች ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ** (Adhoc Board Nomination and Election Committee)" ማለት አዳዲስ የቦርድ አባላት እጩዎችን ጥቆማ እና የምርጫ ሂደት የሚቆጣጠርና የሚመራ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የቦርድ ምርጫ በሚደረግበት ስብሰባ የሚቋቋም ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው፡፡

2.9. "**የማህበሩ ጸሐፊ** (Company Secretary)" ማለት በንግድ ሕጉና በባንኩ የተሻሻለ መመሥረቻ ጽሑፍ መሠረት በባንኩ የቦርድ ስብሰባና በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባዎች ውስጥ በጸሐፊነት የሚያገለግል ባለሙያ ማለት ነው፡፡

2.10. በዚህ የአሰራር ደንብ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠ አገላለጽ ሁሉ የሴት ጾታንም ይጨምራል፡፡

## 3. የአሠራር ደንቡ ዓላማ

3.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ለማካሄድ የሚረዳ የተሟላ መዋቅር ለመመሥረት፣

3.2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣቸውን የቁጥጥር መመዘኛዎች ተግባራዊነት ለማረጋግጥ፣

3.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ግልፅ፣ ፍትሃዊና ትክክለኛ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ፣

3.4. ባንኩን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመቆጣጠርና ስልታዊ አቅጣጫ (Startegic Direction) ለመስጠት የሚያስችል ክህሎት፣ ልምድና ታማኝነት ያላቸው ሰዎች በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት እንዲመረጡ ለማስቻል ነው።

## ክፍል ሁለት
## <u>የቦርድ አባላት ብዛትና ስብጥር</u>

## 4. የቦርድ አባላት ብዛት

የአቢሲንያ ባንክ ቦርድ አሥራ ሁለት (12) አባላት ይኖሩታል።

## 5. የቦርድ ስብጥር

5.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ መዋቅር ሚዛናዊ ውክልናን፣ ብዝሃነትን እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣቸውን መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ መዋቀር ይኖርበታል፡፡

5.2. ቦርዱ በሚከተሉትን የዳይሬክተሮች ምድቦች ይዋቀራል:-

ሀ) **ተጽዕኖ የሌላቸው ባለአክሲዮኖች ውክልና**:- ከጠቅላላ ቦርድ አባላት ውስጥ አንድ ሶስተኛው (1/3) ዕጩዎች የሚጠቆሙት እና የሚመረጡት ተጽዕኖ በሌላቸው ባለአክሲዮኖች ብቻ ይሆናል፡፡

ለ) **አጠቃላይ ውክልና**:- ከጠቅላላ ቦርድ አባላት ውስጥ አንድ ሶስተኛው (1/3) ዕጩዎች የሚጠቆሙት እና የሚመረጡት በሁሉም ባለአክሲዮኖች ይሆናል፡፡

ሐ) **ገለልተኛ ዳይሬክተሮች**:- ከጠቅላላ ቦርድ አባላት ውስጥ አንድ ሶስተኛው (1/3) የሚያዘው በገለልተኛ ዳይሬክተሮች ሲሆን፣ በሥራ ላይ ባለው ቦርድ ተመልምለው ዝርዝሩ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ የሚመረጡት በሁሉም ባለአክሲዮኖች ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## <u>የጊዜያዊ ቦርድ ዕጩዎች ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

### 6. ጊዜያዊ የቦርድ ዕጩዎች ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ

6.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚመረጥበት የባለአክሲዮች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የመጀመሪያው አጀንዳ የጊዜያዊ ዕጩዎች ምልመላና ምርጫ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ማድረግ ይሆናል፡፡

6.2. የጊዜያዊ የእጩዎች ምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ አባላት ባለአክሲዮኖች መሆን የሚኖርባቸው ሲሆን ፤አባላቱ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይመረጣሉ፡፡

6.3 ጊዜያዊ ኮሚቴው ሲቋቋም የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) አምስት (5) አባላት ሊኖሩት ይገባል፡፡

ለ) በሥራ ላይ ያለው ቦርድ አባላት እና የባንኩ ሠራተኞች የጊዜያዊ ኮሚቴው አባል መሆን አይችሉም።

ሐ) ከአባላቱ ቢያንስ ሁለት (2) ተጽዕኖ የሌላቸው ባለአክሲዮኖች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

### 7. የጊዜያዊ ኮሚቴው የሥራ ማብቂያ ጊዜ

7.1. የጊዜያዊ ኮሚቴው ኃላፊነት የድምጽ ቆጠራ እስኪጠናቀቅ እና የምርጫ ውጤት እስኪገለጽ ድረስ ይቀጥላል፡፡ የድምጽ ቆጠራ ሂደቱ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚደረግበት ቀን ካልተጠናቀቀ፤ ኮሚቴው ውጤቱን እስኪያሳውቅ ድረስ በሥራ ላይ ይቆያል፡፡

7.2. የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገው ጊዜ እስከሚቀጥለው የሥራ ቀን ሊራዘም ይችላል፡፡ ኮሚቴው የመጨረሻ የምርጫ ውጤት ካሳወቀ በኋላ የሥራ ጊዜው ይጠናቀቃል፡፡

## ክፍል አራት

## በቦርድ አባላት የዕጩዎች ጥቆማና ምርጫ ሂደት የተለያዩ አካላት

## <u>ተግባርና ኃላፊነት</u>

### 8. በሥራ ላይ ያለው ቦርድ ተግባርና እና ኃላፊነት

8.1. የዕጩዎች ጥቆማ እና ምርጫ ሂደትን በመቆጣጠር ሂደቱ በፍትሃዊነት እና በግልጽነት መከናወኑን ያረጋግጣል፡፡

8.2. የቦርዱ ዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ ያቀረባቸውን የገለልተኛ ዳይሬክተሮች እጩዎችን ብቁነት በመገምገም እና ተስማሚ እና ትክክለኛ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ለጠቅላላ ጉባዔው ምርጫ ያቀርባል፡፡

8.3. አዲስ የቦርድ አባላት ወደ ሥራ በቀላሉ እንዲገቡ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 9. የቦርድ የዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ ተግባርና እና ኃላፊነት

9.1. ለገለልተኛ ዳይሬክተርነት ቦታዎች ዕጩዎችን የብሄራዊ ባንክ መመሪያዎችንንና የባንኩን ስትራቴጂ በመከተል መልምሎ ለቦርድ ያቀርባል፡፡

9.2. የዕጩዎች ምልመላ ሂደት፣ የዕጩዎች ምልመላ መስፈርቶችን፣ የዕጩዎች ግምገማ እና የውሳኔ ሠነዶችን በአግባቡ በመያዝ የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ሹመት ግልጽና ተቀባይነት ያለው ሂደት እንዲሆን ያደርጋል፡፡

9.3. በቦርዱ ውስጥ በገለልተኛ ዳይሬክተርነት እንዲያገለግሉ የሚመለመሉ ዕጩዎች አነስተኛውን የብሔራዊ ባንክ መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡

9.4. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ዕጩዎች ብዛት መመረጥ ካለበት የገለልተኛ ቦርድ አባላት ብዛት ቢያንስ ሁለት እጥፍ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

## 10.የጊዜያዊ የቦርድ ዕጩዎች ምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ ተግባርና እና ኃላፊነት

ጊዜያዊ ኮሚቴው፡-

10.1. የቦርድ አባላት ዕጩዎችን ጥቆማ ሂደት ያመቻቻል፣ ይቆጣጠራል፣

10.2. ለምርጫ የሚቀርቡ የዕጩዎችን ዝርዝር የዘጋጃል፣

10.3. የምርጫ ሂደቱን ያመቻቻል፣ ይቆጣጠራል፣

10.4. የምርጫ ውጤቶችን ይወስናል፣ ይፋ ያደርገል፡፡

## 11.የማህበሩ ፀሐፊ ተግባርና እና ኃላፊነት

የማህበሩ ፀሐፊ በቦርድ አባላት ዕጩዎች ጥቆማ እና በምርጫ ሂደት ውስጥ ያለው ሚና እና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡-

11.1. የቦርድ ዕጩዎች ጥቆማ እና የምርጫ መስፈርቶች የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ከመደረጉ ቢያንስ ከአንድ ወር በፊት ለባለአክሲዮኖች ይፋ መደረጉን ያረጋግጣል። ይህ መረጃ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች ማለትም በጋዜጦች፣ በባንኩ ድረ-ገጽ እና እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መንገዶች በማስታወቂያ መገለጽ አለበት፡፡

11.2. ከላይ የተጠቀሰው መረጃ ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የብቁነት መመዘኛዎች፣ የዕጩዎች ጥቆማ እና ምርጫ በምድቦች ተለይቶ ግልጽ መግለጫ የያዘ መሆን አለበት፡፡

11.3. ስለ ዕጩዎቹ ዝርዝር መረጃ እና የጠቆሟቸው ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር በአግባቡ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

11.4. ለጊዜያዊ ኮሚቴው የአስተዳደራዊ ድጋፍ መስጠት ያለበት ሲሆን፤ ለዕጩዎች ጥቆማ እና ለምርጫ ሂደት አስፈላጊውን ሠነዶች ማዘጋጀት እና ሁሉም የጥቆማና የምርጫ አሠራር መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አምስት
## ውክልና

### 12. በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በተወካይ ስለመሳተፍ

12.1. ባለአክሲዮኖች በጠቅላላ ጉባዔ በተወካይ ለመሳተፍና ድምፅ ለመስጠት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ስለውክልና ተሳትፎ ያስቀመጣቸው ገደቦች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

12.2. አንድ ባለአክሲዮን የራሱን አክሲዮኖች ጨምሮ ከባንኩ የተከፈለ ካፒታል ውስጥ ከ10% በላይ ድርሻ ያላቸውን ባለአክሲዮኖችን መወከል አይችልም፡፡

12.3. በሥራ ላይ ያለው ቦርድ አባል፣ ማንኛውም የባንኩ ሠራተኛ፤ ዋና ሥራ አስፈፃሚ (CEO) እና ማንኛውም ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚ በማንኛውም የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የባለአክሲዮኖች ተወካይ እንዲሆኑ አይፈቀድላቸውም፡፡

### 13. የውክልና ሠነድ ስለማቀረብ

13.1. ሁሉም የውክልና መስጫ ሠነዶች በጽሑፍ መቅረብ አለባቸው።

13.2. የማህበሩ ፀሐፊ የምርጫ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት ሁሉም የውክልና ሠነዶች የአሥር በመቶ (10%) ገደብ ያላለፉ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

## ክፍል ስድስት
## የቦርድ ዕጩዎች ጥቆማ እና የምርጫ ሂደት

### 14. አጠቃላይ

14.1. የቦርድ የዕጩዎች የጥቆማ እና የምርጫ ሂደት ለቦርድ አባልነት ብቁ የሆኑ ዕጩዎችን ለመምረጥ የሚያግዝ ነው። ይህ ሂደት በሥራ ላይ ያለውን ቦርድ፣ የቦርድ የዕጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴን፣ በጠቅላላ ጉባዔው ለዳሬክተሮች ምርጫ ዓላማ በየጊዜው የሚቋቋመውን ጊዜያዊ የዕጩዎች ምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴን እንዲሁም ባለአክሲዮኖችን ያካትታል።

14.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የእጩዎች ጥቆማ እና የምርጫ ሂደት በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በጸደቀ በዚህ የአሰራር ደንብ የሚመራ ይሆናል፡፡

## 15. የገለልተኛ ዳይሬክተሮች ምልመላ

15.1. የቦርድ የእጩዎች ምልመላ እና የክፍያ ኮሚቴ በዚህ ደንብ አንቀጽ 7 ላይ በተጠቀሰው መሠረት ለገለልተኛ ዳይሬክተርነት የመለመላቸውን ዕጩዎች መመረጥ ካለበት የአባላት ብዛት ቢያንስ ሁለት እጥፍ መሆኑን በማረጋገጥ ለቦርዱ ያቀርባል።

15.2. በሥራ ላይ ያለው የዳይሬክተሮች ቦርድ የገለልተኛ ዳይሬክተሮች የእጩዎችን ዝርዝር ለጊዜያዊ የእጩዎች ምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ ያስረክባል፡፡

## 16. የአጠቃላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ፤

16.1. የአጠቃላይ የዳይሬክተሮች እጩዎችን ጥቆማ የጊዜያዊ የዕጩዎች ምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ቀን ከባለአክሲዮኖች ይቀበላል፡፡

16.2. ሁሉም የእጩዎች ጥቆማዎች የሚከተሉትን መረጃዎች መግለፅ አለባቸው፡-

ሀ. የዕጩውን ሙሉ ስም፤ የትምህርት ደረጃ እና የትምህርት መስክ፣ የሙያ ብቁነትና የስራ ልምድ አጭር መግለጫ፤

ለ. ጥቆማውን ያቀረበው የባለአክሲዮን ሙሉ ስም፡፡

16.3. ተገቢውን መስፈርት የሚያሟሉ ባለአክሲዮኖች ራሳቸውን በዕጩነት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## 17. ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውን ድርጅቶች በእጩነት ስለመጠቆም

17.1. ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ ሊመረጥ ይችላል።

17.2. ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት በእጩነት ሲቀርብ የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡-

ሀ. ቦርዱ ላይ ሕጋዊ ሰውነት ያለውን ድርጅት የሚወክል ተፈጥሯዊ ሰው በጥቆማ ሂደት ውስጥ መለየት አለበት፣ ይህ ተወካይ ስለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የወጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

ለ. በጥቆማ ሂደት ውስጥ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ተወካዩን ካልገለፀ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ ተወካይ ምርጫው በተጠናቀቀ በአጭር ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 18. የዕጩዎች ጥቆማ ስለመቀበል

18.1. የጊዜያዊ የዕጩዎች ምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ቀን ዕጩዎችን በሚከተሉት ሦስት የተለያዩ ምድቦችን መሠረት በማድረግ በእያንዳንዱ ምድብ በመለያየት ጥቆማውን ይቀበላል፡-

ሀ. ምድብ 1፡ ከጠቅላላ የቦርዱ አባላት ብዛት አንድ ሦስተኛ (1/3) አባላት የሚሆኑት ዕጩዎች ተፅእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ የሚጠቆሙና የሚመረጡ ይሆናል፡፡

ለ. ምድብ 2፡ ከጠቅላላ የቦርዱ አባላት ብዛት አንድ ሦስተኛ (1/3) አባላት የሚሆኑ ዕጩዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች ያለልዩነት የሚጠቆሙና የሚመረጡ ይሆናል።

ሐ. ምድብ 3፡ ከጠቅላላ የቦርዱ አባላት ብዛት አንድ ሦስተኛ (1/3) አባላት የሚሆኑ ዕጩዎች ለገለልተኛ ዳይሬክተሮች የተያዘ ሲሆን፤ የዕጩዎች ዝርዝር በሥራ ላይ ባለው ቦርድ የሚቀርብ ሆኖ፤ የሚመረጡት በሁሉም ባለአክሲዮኖች ይሆናል፡፡

18.2. ለምርጫ የሚቀርቡ የቦርድ እጩዎች ብዛት ከእያንዳንዱ ምድብ የሚመረጡትን የቦርድ አባላት ብዛት ሁለት (2) እጥፍ ይሆናል፡፡

18.3. ጊዜያዊ ኮሚቴው የዕጩዎች ጥቆማ መቀበል ከመጀመሩ በፊት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጡትን የብቁነት እና የተስማሚነት መስፈርቶችን ያሳውቃል፤ ባለአክሲዮኖችም እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዕጩዎችን መጠቆም አለባቸው፡፡

18.4. ጊዜያዊ ኮሚቴው በዚህ የአሰራር ደንብ አንቀፅ 18 መሠረት የዕጩዎችን ጥቆማ ከባለአክሲዮኖች ይቀበላል፡፡ ዕጩዎችም በምርጫው ለመወዳደር ዝቅተኛውን የብሔራዊ ባንክ መስፈርት ማሟላታቸውንና ፈቃደኛ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

## 19. ለምርጫ የሚቀርቡ የዕጩዎች ዝርዝር

19.1. ጊዜያዊ ኮሚቴው ለምርጫ መቅረብ ያለባቸው የዕጩዎች ቁጥር በየምድቡ መጠቆሙን ካረጋገጠ በኋላ ጥቆማውን በተቀበለበት ቅደም ተከተል መሠረት የእያንዳንዱን ምድብ የዕጩዎች ዝርዝር ያዘጋጃል።

19.2. እያንዳንዱ ዕጩ በጉባዔው ላይ ራሱን ለማስተዋወቅ እና በቦርድ ውስጥ ለማገልገል ፍላጎትና ቁርጠኝነት ያለው ስለመሆኑ እንዲገልፅ ዕድል ይሰጠዋል።

19.3. ጊዜያዊ ኮሚቴው የዕጩዎች ዝርዝር በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ አዳራሽ ውስጥ በግልፅ እንዲታይ በማድረግ ባለአክሲዮኖች በምርጫ ጊዜ የዕጩዎችን ዝርዝር በግልጽ እንዲያውቁ ያደርጋል።

## 20. ድምፅ የመስጠት ሥነ-ሥርዓት

20.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ እያንዳንዱን ምድብ ለይቶ ለየራሱ የምርጫ ምድብ ድምጽ ይሰጥበታል። በእያንዳንዱ ምድብ ያሉ ዕጩዎችን የመምረጥ መብቶች በአንቀጽ 18 ሥር በተገለጸው መሠረት ይሆናል።

20.2. ባንኩ ተፅእኖ ፈጣሪ የሆኑ ባለአክሲዮኖች ከሌሉት፣ በምድብ 1 ላይ የተዘረዘረው ገደብ አይተገበርም፡፡ በመሆኑም ሁሉም ዳይሬክተሮች በሁሉም ባለአክሲዮኖች ይመረጣሉ፡፡

## 21. የድምጽ መስጫ ወረቀቶች

21.1. በእያንዳንዱ የዕጩዎች ምድብ (ምድብ 1፣ ምድብ 2፣ ምድብ 3) ተብሎ በተለየ መልኩ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ይዘጋጃሉ። እያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ወረቀት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

ሀ. የሚመረጡትን ዕጩዎች ስም ለመጻፍ የሚሆን ቦታ ወይም መስመር፤

ለ. የባለአክሲዮን ሙሉ ስም፣ የባለአክሲዮን መለያ ቁጥር (Shareholder ID) እና ፊርማ፤

ሐ. የባንኩ ማህተም፡፡

21.2. ጊዜያዊ ኮሚቴው ከማህበሩ ጸሐፊ እና ከድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር በመተባበር የድምፅ መስጫ ወረቀቶች በትክክል ለባለአክሲዮኖች እንዲደርሱ እና ድምፅ ከተሰጠባቸው በኋላ በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ያደርጋል፡፡

## 22. ድምጽ ስለመስጠት፡-

22.1. ባለአክሲዮኖች መምረጥ የሚፈልጓቸውን ዕጩዎች ሙሉ ስም በተዘጋጀው የድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ ይጽፋሉ፤ ይፈርማሉ፤ የሞሉትን የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ለመሰብሰብ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ያስገባሉ፡፡

22.2. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ባለው መብት መሠረት ብቻ ድምጽ ይሰጣል (ለምሳሌ፡- ምድብ 1 ውስጥ ያሉ ዕጩዎችን ለመምረጥና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉት ተፅእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ብቻ ናቸው)፡፡

## 23. ድምጽ የተሰጠባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የሚሰበሰቡበት መንገድ፡-

23.1. ድምጽ የተሰጠባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመሰብሰብ የሚሆኑ ሳጥኖች በባንኩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በቅድሚያ ተዘጋጅተው እና ባዶ ተደርገው ወደ ጠቅላላ ጉባኤው ቦታ ይመጣሉ፡፡

23.2. ጊዜያዊ ኮሚቴው እነዚህ ሳጥኖች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ይቆጣጠራል፡፡

23.3. ባለአክሲዮኖች የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ሞልተው እንዳጠናቀቁ የባንኩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ሳጥኖቹን ወደ ስብሰባ አዳራሽ ይዘው በመግባት የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ለመሰብሰብ ሳጥኖቹን ያዞራሉ፡፡

23.4. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የመረጣቸውን እጩዎች ስም በትክክል ሞልቶና ፈርሞ ያጠናቀቀውን የድምፅ መስጫ ወረቀት በቀጥታ ሳጥኖቹ ውስጥ ያስገባል፡፡

23.5. ጊዜያዊ ኮሚቴው በዚህ ሂደት ውስጥ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች የአሰባሰብ ደህንነትና ሥነ-ሥርዓት መጠበቁን እና በየምድቡ ተለይቶ መሰብሰቡን ያረጋግጣል፡፡

## 24. የድምጽ ቆጠራ፡-

24.1. የድምጽ መስጠት ሂደቱ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጊዜያዊ ኮሚቴው ከማህበሩ ጸሐፊ እና ከድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር በመተባበር የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን ይጀምራሉ። የድምጽ ቆጠራው ለዚህ ተዘጋጅቶ በተለይ የተዘጋጀ የኮምፒዩተር ሥርዓት በመጠቀም ይካሄዳል፡፡

24.2. **የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ማጣሪያ፡-** የተሞሉ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በሚከተሉት ምክንያቶች ይሰረዛሉ ወይም ዋጋ ያጣሉ፡፡

ሀ. በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ የባንኩ ማህተም ካላረፈ፤

ለ. የባለአክሲዮን ስም፣ የባለአክሲዮን መለያ ቁጥር ወይም ፊርማ ካልተካተተ፤ ወይም

ሐ. የተጻፈው ጽሁፍ የማይነበብ ወይም የማይታይ ከሆነ

24.3. **ለምርጫ የተሰጠ ድምጽ ስለመመዝገብ እና ስለተሰረዙ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ማብራሪያ ስለመስጠት፡-** በድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ጊዜያዊ ኮሚቴው የሚከተሉትን ያከናውናል፡-

ሀ. እያንዳንዱ ዕጩ ያገኘውን የድምጽ ቁጥር ይመዘግባል፤

ለ. የተሰረዙ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛትና ምክንያታቸውን ይመዘገባል፤

ሐ. የተሰረዙትን የድምፅ መስጫ የምርጫ ወረቀቶች ላይ የተሰረዘበት ምክንያት በራሱ በሰነዱ ላይ በግልጽ ይጽፋል፡፡

## 25. የምርጫ ውጤት ስለማሳወቅ እና የውጤት ማስተካከያ ስለማድረግ

25.1. **የምርጫ ውጤት በተገኘ ከፍተኛ ድምጽ መሠረት የሚወሰን ስለመሆኑ፡-**

ከእያንዳንዱ ምድብ (ምድብ 1፣ ምድብ 2፣ ምድብ 3) በተሰጡ ትክክለኛ ድምጾች ውስጥ ከፍተኛውን የድምጽ ቁጥር ያገኙ እጩዎች እንደተመረጡ ይቆጠራል፡፡

25.2. **የቦርድ የስብጥር መስፈርት መሟላቱን ስለመመርመር፡-**

የተመረጡ ዳይሬክተሮች ዝርዝር ይፋ ከመደረጉ በፊት፣ ጊዜያዊ ኮሚቴው በባለአክሲዮኖች ድምጽ በተሰጠው መሠረት የባንኩ ቦርድ ስብጥር የብሔራዊ ባንክ መስፈርቶችን እንዲያሟላ ጥረት ያደርጋል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

ሀ. በብሔራዊ ባንክ መስፈርት መሠረት ተፈላጊው የሙያ ችሎታዎችና ልምድ ስብጥር መሟላቱን፤ እና

ለ. ቢያንስ ሁለት ሴቶች በዳይሬክተሮች ቦርድ መካታተቻውን ያረጋግጣል፡፡

25.3. **አስፈላጊ ማስተካከያ፡-**

የተመረጠው ቦርድ የብሔራዊ ባንክ የስብጥር መስፈርቶች አለመሟላቱን ኮሚቴው ካረጋገጠ፣ ጊዜያዊ ኮሚቴው በተገቢው ምድብ ውስጥ ድምጽ ካገኙ ከቀሩት ዕጩዎች መካከል በመምረጥ አስፈላጊ ማስተካከያዎችን በማድረግ መስፈርቶቹ እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡ ማስተካከያ ካስፈለገ ያስፈለገበት ምክንያት በግልጽ ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

## 26. የእኩል ድምጽ ውጤት ሲኖር የሚተገበረው የመፍትሄ ሂደት፡

26.1. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ዕጩዎች በአንድ ምድብ ውስጥ ተመሳሳይ የድምጽ ቁጥር ካገኙ፣ ጊዜያዊ ኮሚቴው የቦርዱ ስብጥር የብሔራዊ ባንክ መስፈርትን ለማሟላት በሚያስችል ሁኔታ የሚፈለገው ክህሎት፣ ልምድ ወይም ጾታዊ ልዩነት በማወዳደር ቀሪ ክፍተት ለመሟላት በሚያግዝ ሁኔታ ከዕጩዎቹ በመምረጥ መፍትሄ ይሰጠዋል፡፡

26.2. የቦርዱ ስብጥር የብሔራዊ ባንክ መስፈርት ክፍተት ከሌለበት፣ እኩል ድምፅ ያገኙት ዕጩዎች በዕጣ ይለያሉ፡፡

26.3. ጊዜያዊ ኮሚቴው የእኩል ድምጽ ላይ የሰጠውን ውሳኔ እና ምክንያት በቃለ-ጉባዔ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

## 27. የምርጫ ውጤት ስለማሳወቅ፡

ጊዜያዊ ኮሚቴው የመጨረሻ የምርጫ ውጤት ዝርዝር ለባለአክሲዮኖች እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡ የምርጫ ውጤት ዝርዝሩ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ. ለእያንዳንዱ ምድብ (ምድብ 1፣ ምድብ 2፣ ምድብ 3) የተመረጡ ዳይሬክተሮች ሙሉ ስምና ያገኙትን ድምጽ ብዛት፣

ለ. በእያንዳንዱ ምድብ  ድምጽ ተሰጥቷቸው ያልተመረጡ ተጠባባቂ ዕጩዎች ሙሉ ስምና ያገኙትን ድምጽ ብዛት፣

ሐ. የብሔራዊ ባንክ የስብጥር መስፈርት ለማሟላት የተደረገ ማስተካከያ ካለ በግልጽ ከነምክንያቱ ከምርጫ ውጤቱ ጋር መገለጽ ይኖርበታል፡፡

## 28.የተጠባባቂዎች ዝርዝር

ድምጽ ተሰጥቷቸው ያልተመረጡ ዕጩዎች ሙሉ ስምና ያገኙት ድምጽ ብዛት በየምድባቸው በተጠባባቂዎች ዝርዝር ተመዝግቦ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡ ይህም የተጠባባቂዎች ዝርዝር በቦርዱ የስራ ዘመን ውስጥ ክፍት የቦርድ መደቦች ሲኖሩ ብቁ የሆኑ ዕጩዎች ባገኙት ድምጽ እና የብሔራዊ ባንክ የስብጥር መስፈርቶች መሠረት ክፍት ቦታዎችን ለመሙላት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

## 29. የምርጫ ውጤት በጉባዔው ቦታና ቀን ማሳወቅ አለመቻል፡

ከጊዜ ማነስ ወይም በቴክኒክ ምክንያት የተነሳ የድምጽ ቆጠራ ሂደት በጠቅላላ ጉባዔው በተካሄደበት ቀን ላይ ካልተጠናቀቀ፣ ውጤቱ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በባንኩ ዋና መ/ቤት የማስታወቂያ ቦርድ ላይ እንዲለጠፍና በባንኩ ድረ-ገጽ ላይም እንዲለጠፍ ይደረጋል፡፡

## 30. የምርጫ ሂደት ሠነዶች ስለማስቀመጥ፡

30.1. የሁሉም የምርጫ ውጤቶች በእያንዳንዱ ምድብ ያሉ ዕጩዎች ያገኙት የድምጽ ቁጥር፣ የድምጽ እኩልነት ሲኖር የተወሰነው ውሳኔ ምክንያት፣ የብሔራዊ ባንክ ስብጥር መስፈርትን ለማሟላት የተወሰነ ውሳኔ እና

የምርጫ ሂደቱ ትክክለኛነትን የሚያረጋግጡ ሠነዶች በአግባቡ መቀመጥ አለባቸው፤ ዝርዝር ሁኔታው በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ቃለ-ጉባዔ ውስጥ ይመዘገባል፡፡

30.2. የማህበሩ ጸሐፊ ድምጽ የተሰጠባቸውን ወረቀቶች እና ተያያዥ የምርጫ ሠነዶች ለወደፊት ሲፈለጉ ማግኘት እንዲቻል አድርጎ ያስቀምጣል፡፡

30.3. የማህበሩ ጸሐፊ የምርጫ ውጤቱና የዳይሬክተሮች ሹመት በብሔራዊ ባንክ እንዲፀድቅ ለብሔራዊ ባንክ ይልካል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 31. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሕጎችና መመሪያዎች ይህን የአሠራር ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

### 32. ማሻሻያ

ይህ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ማስፈፀሚያ የአሰራር ደንብ በዳይሬክተሮች ቦርድ ማሻሻያ ሊደረግበት የሚችል ሲሆን፣ ማሻሻያው ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ መጽደቅ አለበት፡፡

### 33. የተሻረ ደንብ

የባለአክሲዮኖች 23ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ህዳር 13 ቀን 2012 ዓ.ም አጽድቆት የነበረው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ማስፈፀሚያ የአሠራር ደንብ ተሽሮ በዚህ የአሠራር ደንብ ተተክቷል፡፡

### 34. አሠራር ደንቡ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ የአሠራር ደንብ በጠቅላላ ጉባዔው ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡